# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 306 መጋቢት 12 2006

**ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ በልማት ስም በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽመውን የማፈናቀል ዘመቻ ማስቆም የኢያንዳንዳችን ግዴታ ነው ብሎ ያምናል። ሕዝባችን በጨለማ እየተሰቃዬ ከደጃችን የሚመረት የመብራት ኃይል ወደ ጎረቤት አገር እየተላከ ለማይጠረቃው የወያኔ ሃብት የማጋበስ ጥማት ማርኪያ መሆን ማስቆም የምንችለው እኛው ብቻ ነን።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ከግብር ጋር ተያይዞ በተነሳ ውዝግብ አርሶ አደሮች በፋሽስቱ ወያኔ ታጣቂዎች መገደላቸው ተሰማ

ነገሩ የተከሰተው ከወደ ጎጃም ሲሆን የፋሽስቱ ወያኔ ታጣቂዎች ከሃቅም በላይ የተጣለውን የግብር ሂሳብ በማናለብኝነትና በትዕቢት እናስከፍላለን በሚል ከእርሻ ላይ በሬ ለመፍታት ባደረጉት ሙከራና፣ በሬዎቼን ከቀንበር ላይ አላስፈታም ባለ አርሶ አደር መካከል በተፈጠረ ውዝግብ ነው የአምስት ሰዎች ህይዎት የጠፋው። በግጭቱ ከሞቱት መካከል ሶስቱ የአንድ ቤተሰብ አባላት መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን የቤቱ አባዎራን አርሶ አደር በሪሁን ፈንታን ጨምሮ ባለቤቱና የመጀመሪያ ልጁ በፋሽስቱ ወያኔ ታጣቂዎች ተገድለዋል።

በተያያዘ ዜና ዘራፊው የወያኔ ቡድን በመላ ሃገሪቱ የሚገኙ አርሶ አደሮች ማዳበሪያ እና ምርጥ ዘር ወስዳችሁ ግብር እና የማዳበሪያና የምርጥ ዘር እዳችሁን አንክፍልም ብላችኃል በሚል መሰረት የለሽ ክስ እየታሰሩና ስቃይ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በግብርና መሰል የፋሽስቱ ወያኔ መሰረት የለሽ ውንጀላ ምክንያት በኑሮና በዕድሜ የተጎሳቆሉ አርሶ አደሮች ታስረው ይንገላታሉ፤ ከብቶቻቸውን ከቤታቸው እንዲሁም ከቀንበሩ ፈተው ይወሰዳሉ፣ ድብዳና ግድያም ይፈጽማል ሲሉ በፋሽስቱ ወያኔ ታጣቂዎች እየደረሰባቸውን ያለው ግፍ አጋልጠዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ፋሽስቱ ወያኔ እንደፈልግሁ ብቀጠቅጠውና ብገርፈው አርሶ አደሩ ይደግፈኛል እያለ ይሳለቅበት የነበረው ይህ ጭቁን ገበሬ በአገዛዙ ላይ ፊቱን ማዞሩ በወያኔ መንደር ከፍተኛ ውጥረትን ማንገሱ የተሰማ ሲሆን ፋሽስቱ ወያኔ ይህንን ውጥረት ተከትሎ መጭው የ 2007 ምርጫ ተብየ ድራማ እስኪያልፍ ድረስ በግብር ስም እያደረገ ያለውን ዝርፊያ ለመተው እንደወሰነ መረጃዎች ያመለከታሉ።

የፋሽስቱ ወያኔ የዘራፊ ቡድን በግብር ሽፋን እያካሄደ ባለው መጠነ ሰፊ ዝርፊያ የተማረሩ በርካታ አርሶ አደሮች ንብረቶቻቸው በጉጅሌው ወያኔ የተወሰደባቸውን ጨምሮ እየተሰደዱና በድንበር የሚነቀሳቀሱ የተቃዋሚ ሃይሎችን ጋር አገዛዙን ለመዋጋት እየተቀላቀሉ እንደሚገኙም ታውቋል።

## በኩዌት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ጭንቀትና ስቃይ ውስጥ ናቸው!

በወያኔዋ ኢትዮጵያ ዉስጥ የስራ እድል ባለመኖሩ ስራ ፍለጋ አገራቸዉን እየለቀቁ ወደ አረብ አገሮች በሚጓዙ ኢትዮጵያዉያን ላይ ከፍ ጭንቀት ላይ እንደሚገኙ ላይ እንደሚገኙ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ኢሳት ዘገበ። በኢሳት ዘገባ መሠረት ለውጥረቱ መንስኤ መሆኑ የተነገረው አንዲት ኢትዮጵያዊት አንድ የአገሪቱን ባለስልጣን ልጅ መግደሉዋን ተከትሎ ሲሆን ኢትዮጵያዊቷ ግድያውን የፈጸመችበትን ትክክለኛ ምክንያት ለማወቅ ባይቻልም፣ ገዳዩዋን በቅርብ እናውቃለን ከሚሉ ወገኖች የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ከሶስት አመት በፊት ወደ ኩዌት በገባች በመጀመሪያው ወር ላይ በአሰሪዋ ልጅ መደፈሩዋን ለመበቀል በሚል የባለስልጣኑን ልጅ ለመግደል እንደተነሳሳች መግለጿን ኢትዮጵያውያን ይናገራሉ።

ግድያውን ተከትሎ የሟች አክስት የሆነች አንዲት ማንነቱዋ ያልተገለጸ አሰሪ ከአራት ኢትዮጵያውያን የቤት ሰራተኞች መካከል እጣ በማውጣት አንደኛዋን ኢትዮጵያዊት በአሰቃቂ ሁኔታ በማረድ የአክስቷን ልጅ ሞት መበቀሉዋን ኢትዮጵያውያን በፎቶ ግራፍ አስደግፈው ለኢሳት የላኩት መረጃ ያሳያል። እንደ ኢሳት ዘገባ በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያውያን ከቤት ለመውጣት እንዳልቻሉ፣ ከቤት ቢወጡ ተይዘው እንደሚታሰሩ ወይም የበቀል ሰለባ እንደሚሆኑ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሱ በደሎችን የሚከራከር አካል እና የወግኖቹ ሰቆቃ የሚያሳስበው ኤምባሲ ባለመኖሩ ለአሁኑ ወንጀል መፈጸም እና ስጋት መንስኤ እንደሆነ የጠቆሙት ኢትዮጵያውያኑ፤ ኢትዮጵያውያንን ለማሰባሰብ በሚል በጉጅሌው ወያኔ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ እንኳ ምንም ለወገኖች ደንታ በሌላቸው የወያኔ ቅጥረኞች ( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## በወያኔ በግፍ የታገቱት የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አባላት በዋስ መለቀቃቸው ተሰማ

የሴቶች 5000 ሜትር ሩጫ ላይ ለነፃነት እንሩጥ በሚል መርህ በሩጫው ላይ በመሳተፍ በርካታ ፖለቲካዊና መህበራዊ ጥያቄዎችን ያነሱ የሰማያዊ ፓርቲ የሴቶች ጉዳይ ሀላፊዎችና አባላት እንዲሁም በስፍራው ንብረቶቻቸውን ይጠብቁ የነበሩ ሁለት የፓረቲው ከፍተኛ አመራሮች በጉጅሌው ወያኔ ፖሊሶች ታፍሰው መታሰራቸው ይታወሳል። በሩጫው ላይ ከተነሱ ጥያቄዎችና መፈክሮች መካከል ርዕዮትና ሌሎች የህሊና እስረኞች ይፈቱ፣ መብትን መጠየቅ አሸባሪነት ከሆነ አሸባሪዎች ነን፣ ውሃ ናፈቀን፣ መብራት ናፈቀን፣ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ፣ ውሸት ሰለቸንና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

የጉጅሌው ወያኔ የካንጋሮ ፍርድ ቤት ወጣቶችን በወንጀለኝነት ለመክሰስ የሚያበቃ በቂ ማስረጃ ባለመገኘቱ ለ11 ቀናት በውዝግብ ካጉላላ በኋላ በዋስ እንዲለቀቁ መወሰኑ ተሰምቷል። የታሳሪዎቹ ጠበቃ አቶ አለሙ ጎቤቦ ደምበኞቻቸው ያለ ዋስትና እንዲለቀቁና መዝገቡ እንዲዘጋ ቢከራከሩም የጉጅሌው ወያኔ ፖሊስ ክስ እመሰርታለሁ በማለቱ የካንጋሮው ፍርድ ቤት እያንዳንዳቸው የገንዘብ እንዲሁም የአዲስ አበባ ቀበሌ መታወቂያ ያለው ሰው በማቅረብ በዋስ እንዲፈቱ መወሰኑን ከምንጮቻችን ለማረጋገጥ ችለናል።

## ሀረር ከተማ በሳምንት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የእሳት ቃጠሎ ደረሰባት

ባለፈው መጋቢት 30 እኩለ ሌሊት አካባቢ በሀረር ከተማ በተለምዶ መብራት ሃይል በሚባለው የገበያ መነሃሪያ አካባቢ የተነሳው የእሳት ቃጠሎ ያወደመው የሕዝብ ንብረት የፈጠረው ከፍተኛ የሃዘን ስሜት ገና ሳይበርድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ቅዳሜ መጋቢት 6 በዚሁ በሀረር ከተማ ሲጃራ ተራ በሚባለው አካባቢ ለሁተኛ ጊዜ ሌላ የእሳት አደጋ መከሰቱና በሀላፊነት የሚጠየቅ አካል መጥፋቱ የከተማውን ኗሪ በከፍተኛ ሁኔታ ማሳዘኑ እየተነገረ ነው።

ባሁኑ ሰአት ክልሉን ወክሎ ያለው የወያኔ ቡድንም ሆነ በፌደራል ደረጃ የተቀመጡት የሕወሃት ቁንጮዎች ምንም እንደማያስቡልን እየተገነዘብን ነው የሚሉት የከተማው ኗሪዎች፤ በቃጠሎው ንብረታችን የወደመውና የተጎዳነው እኛ ሆነን እያለን ሃብታችንን በካሳም ሆነ በሌላ በማንኛውም መንገድ ለመተካት በመሞከር ፋንታ ተጎጅዎችን አስሮ እኛ ነን እሳት ያስነሳን ብላችሁ ፈርሙ እያሉ ማጉላላት ከውጭ ከመጣ ወራሪ ሃይል እንኳ የማይጠበቅ ነውር ነገር ነው በማለት በማማረር ላይ እንደሆኑም ተጠቁሟል። አንዳንድ የከተማው ኗሪዎች እንደሚሉት ቃጠሎው የደረሰባቸውን ቦታዎች ለወያኔ ተላላኪዎች ለማስረከብ በማሰብ ቃጠሎዎችን የፈጸመው ራሱ የከተማው የወያኔ ቡድን እንደሆነ አባዛኛው ሕዝብ እንደሚያምንም ሳይሸሽጉ በማጋለጥ ላይ እንደሆኑም ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባና በሌሎችም ታላላቅ ከተሞች የተቀነባበሩ የቦንብ ፍንዳታዎችን በንጹሃን ዜጎቻችን ላይ በማፈንዳት ሌሎችን በሀሰት መወንጀሉ ባንዳንድ ዓለማቀፍ ሚዲያዎች የተጋለጠበት ፋሽስት ወያኔ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔ ጄኔራሎች እርስ በርሳቸዉ እየተተራመሱ መሆኑ ተሰማ

ከሕወሃት አባል ወታደሮች በቀር ለማንም ወታደራዊም ሆነ የሲቢል ስልጣን ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን የገፋው ሕወሃት በራሱ ጄኔራሎች መካከል ሌላ አዲስ የጥቅምና የስልጣን ግፊያ መፈጠሩ እየተዘገበ ነው። ከዚህ በፊት የሚፈራቸውን የተለያዩ ወታደራዊ ቁንጮዎቹን በስልጣን ስም ወደ ሲቪልነት የቀረው ሕወሃት አሁንም ይህንኑ እንቅስቃሴ በአማራና አሮሞ ከፍተኛ ወታደራዊ ሃላፊዎች ላይ ሊፈጽም እንደሚችል ነጋዴው ሰሞራ ቅርብ የሆኑ ምንጮች ጠቆሙ።

የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ለስልጣኔ ያሰጉኛል የሚላቸውን የተለያዩ የአማራና የኦሮሞ ሃላፊዎች ከሰልጣን በማባረር፣ ከሶ ዘብጠያ በማውረድና በዚህም በዚያም ብሎ በማሰደድ የሚታወቀው ሕወሃት ሰሞኑንም ሌላ ዙር ጥቃት በወታደሩ ሰፈር ሊጀመር እንደሆነ የሚጠቁሙ ምንጮች እየተሰሙ ነው። በተለይም አማራን ወክሎ ያለው ብቸኛው ጄኔራል አበባውና ሌሎችንም ከሻንበልነት ማእረግ በላይ የሚገኙ የሁለቱ አንጋፋ ብሄሮች አባል ወታደሮችን በሰበብ አስባቡ ከጫወታ ውጭ ለማድረግ እቅዱ ተሰርቶ ማለቁን ውስጥ አዋቂ መንጮች አረጋግጠዋል።

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ከሆነ ጄኔራሎችን ማስወገዱ ከውሳኔ የደረሰው ወታደሩ በከፍተኛ ችግርና መከራ ውስጥ ከሀገር ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## “ውሃ፣ መብራት፣ ኔትዎርክ የለም ፤ ኑሮ ከበደን”

### ሰሚ ጆሮ ያጣ የሕዝብ እሮሮ

“ውሃ የለም፤ መብራት፤ ኔትዎርክ የለም፤ መብት የለም፤ ፍትህ የለም፤ ኑሮ ከበደን” እያሉ ስለኑሮዓቸው የተሰማቸውን በሀቅ የተናገሩ ልጃገረዶች በጋጠወጥ የህወሓት ካድሬዎችና ታጣቂዎች እጅ መከራና ስቃይ እየደረሰባቸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነዚህ ለጋ ወጣቶች ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ በዝምታ ያልፋል ተብሎ አይታመንም።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮን ጨምሮ በወያኔና የጥቅም ተጋሪዎቹ ሥር የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙሃን በየዕለቱ ያለማቋረጥ ከሚዘገቡት የልማትና የዕድገት ዘገባዎች ከፍተኛውን ስፍራ የሚይዘው በአገራችን ውስጥ እየተሠሩ ስላሉ ትላልቅ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግንባታዎች፤ በየከተማው ስለተዘረጉ የውሃ መስመሮች፤ የስልክ አገልግሎት ለማዳረስ ስለተወሰዱ እርምጃዎች፤ ስለ ረጃጅም የባቡር መስመሮች ግንባታ እና ስለ አገር አቋራጭ የመንገድ ሥራዎች የሚቀርቡ የተጋነኑ ዘገባዎች ናቸው።
እነዚህ የልማት አውታሮች ግንባታ በአብዛኛው የሚካሄዱት ከምዕራባዊያን መንግሥታት በሚሰጡ የገንዘብ እርዳታና ዕዳው ለልጅ ልጆቻችን በሚተርፍ አለም አቀፍ የገንዘብ አበዳሪ ድርጅቶች ወለድ እያስከፈሉ በሚሰጡት የረጅም ጊዜ ክፍያ ብድር እንደሆነ ግልጽ ነው።

ወያኔ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 23 አመታት በድህነት ቅነሳና የልማት ማስፋፊያ ስም ከአለም አቀፍ ኅብረተሰብ የተቀበለው የገንዘብ መጠን ሲሰላ ኢትዮጵያ አገራችን እንደ አገር ከተመሰረተችበት ዘመን ጀምሮ በብድርም ሆነ በእርዳታ ስም ይህንን ያህል መጠን ገንዘብ አግኝታ እንደማታውቅ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይናገራሉ ። በዚህም መሠረት ገንዘቡ በአግባብ ሥራ ላይ ውሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ አገራችን የትና የት በደርሰች ነበር እያሉ የሚቆጩ የአገሪቱ ልሂቃንና ቅን አሳቢ ዜጎች ቁጥር ቀላል አይደለም ።

የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት ከ3 አመት ገደማ በፊት ይፋ ባደረገው አንድ መረጃ ወያኔ ሥልጣን በተቆጣጠረባቸው የመጀመሪያዎቹ 9 አመታት ብቻ ከ11.5 (አሥራ አንድ ነጥብ አምስት ) ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ በህገወጥ መንገድ ከአገር አሸሽቶ በምዕራባዊያን አገሮች ባንኮች ደብቆአል ። ይህ ከደሃው ጉሮሮ ተቀምቶ በባለሥልጣናቱ የተዘረፈና በህገወጥ መንገድ ከአገር የሸሸው 11.5 ቢሊዮን ዶላር በትክክል ልማት ላይ ውሎ ቢሆን ኖሮ ወያኔዎች "ባለ ራዕዩ መሪያቸን" በሚሉት ዘረኛው መለስ ዜናዊ ሥም ለመሰየም ደፋ ቀና የሚሉትን ጅምር "የህዳሴ ግድብ" አይነቱን ሁለት ግዙፍ ግድቦችን በመገንባት የአገሪቷን ገጽታ አበላሽቶ የኖረውን ረሃብ ከምንጩ ማጥፋት ይቻል ነበር።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአገሪቱ የሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ፤ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ "ውሃ የለም፣ መብራት የለም፣ ኔትዎርክ የለም። የሚላስ የሚቀመስ ነገር ማግኘት ተስኖናል፤ ኑሮ ከአቅማችን በላይ ሆኖአል። ትዳር መስርተንና ልጆች ወልደን እያሳደግንበት ካለው የደሃ ጎጆዎቻችን በቀበሌ ካድሬዎች ትዕዛዝ ቤቶቻችን በዶዘር ላያችን ላይ እንዲፈርስ ተደርጎ ሜዳ ላይ ተበትነናል። ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ጊዜ ጀምሮ እንገለገልበት ከነበረው የእርሻ ማሳችንና የግጦሽ መሬታችን ተነቅለን ዓይኖቻችን እያዩ ከህንድ፣ ከቻይናና ከአረብ አገር የመጡ ከበርቴዎች መሬታችንን ተቀራምተውታል። አቤት የምንልበት አጣን። ኑሮ መሮናል!!!" የሚሉ እሮሮዎች የወያኔ አፈና የፈጠረውን የፍርሃት ዝምታን ሰብሮ ከአጥናፍ አጥናፍ እየተሰማ ነው።

ይህንን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና እየከረረ የመጣውን የሕዝብ እሮሮ ለማዳመጥ ጆሮ ያልፈጠረበት የዘረኛው ህወሓት አገዛዝ ግን “ነጋ ጠባ የሚደሰኮረው ልማት ምድር ላይ ጠብ አላለልንም፤ መሠረታዊ ችግሮቻችን ከመፍታት ይልቅ እያባባሰ ያለው ምን የሚሉት ልማት ነው?” ብሎ የጠየቀውን ሁሉ “ፀረ-ልማት፣ ፀረ-ሰላም፣ ሽብርተኛ” የሚል ስም እየለጠፈበት ማሰር ማዋከብና ማሳደድ የዘወትር ተግባሩ አድርጎታል።

በቅርቡ አዲስ አበባ ላይ አለም አቀፍ የሴቶች በዓል ሲከበር ይኸው የሕዝብን ብሶት ባስተጋቡት ወጣት እህቶቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ የዚህ የወያኔ አፈና እርምጃ ማሳያ ነው። “ብሶት የፈጠረኝ ነኝ” የሚለው ህወሓት፤ ብሶት እሱን ብቻ ፈጥሮ የመከነ ይመስለዋል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ እያካሄድኩ ነው በሚላቸው ትላልቅና ትናንሽ ግንባታዎች መጠነ ሰፊ ብዝበዛና ዘረፋ እያካሄደ መሆኑን የሚያጋልጡ በቂ መረጃዎች አሉት። የወያኔ ልማትና እድገት ማሳያ ተደርጎ ከሚጠቀሱ የኮንዶሚኒዬም ቤቶች ግንባታ አንስቶ በመላው አገሪቱ ለሚሠሩ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በሙሉ የሚያስፈልጉ የግንባታ ዕቃዎች ስምንቶ፤ አሸዋና ብረታ ብረት የመሳሰሉትን የሚያቀርቡት በባለሥልጣናቱ ንብረትነት የሚታወቁና በቤተሰቦቻቸው ወይም የቅርብ ዘመዶቻቸው ስም የሚተዳደሩ የግል ድርጅቶች ናቸው። የግንባታዎቹን ሥራ ደግሞ የሚያካሂዱት በወያኔ ንብረትነት የሚታወቁ የኢፈርት ሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች ናቸው። በዚህ አይነት ኮንትራት ሰጪ፤ ኮንትራት ተቀባይና ዕቃ አቅራቢ በመሆን በሚበዘበዘውና በሚዘረፈው የሕዝብ ሃብት የወያኔ ሹማምንትና ግብረ አበሮቹ እስከ ልጅ ልጆቻቸው በልተው የማይጨርሱትን ሃብት አግበስብሰዋል።

ይህ አልበቃ ብሎአቸውም አይናቸው ያረፈባቸው ቁልፍ የከተማ ቦታዎች ላይ የሰፈረውን ደሃ ሕዝብ በማፈናቀልና ጎዳና ላይ በመበተን ረጃጅም ፎቆችን እየሰሩ በማከራየት ሥራ ላይ ተጠምደዋል። ከአመታት በፊት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአነስተኛ ንግድ የተሰማሩ በርካታ ዜጎች የያዙትን ቦታ ለማስለቀቅ ሆን ተብሎ ንብረታቸው በእሳት እንዲወድም ተደርጎአል። በሕይወት ዘመናቸው ያፈሯት ሃብት በእሳት እንዲጋይባቸው የተደረጉ ዜጎች አቤት የሚሉበት ስላልነበራቸው ሥራ አጥና የጎዳና ተዳዳሪ ለመሆን ተገደዋል። ባለፈው ሁለት ሳምንት ተመሳሳይ እርምጃ ሀረር ከተማ ውስጥ በአነስተኛ ንግድ በተሰማሩት ወገኖቻችን ላይ ደርሶ እንባ ሲራጩ ተመልክተናል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ በልማት ስም በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽመውን የማፈናቀል ዘመቻ ማስቆም የእያንዳንዳችን ግዴታ ነው ብሎ ያምናል። ሕዝባችን በጨለማ እየተሰቃዬ ከደጃችን የሚመረት የመብራት ኃይል ወደ ጎረቤት አገር እየተላከ ለማይጠረቃው የወያኔ ሃብት የማጋበስ ጥማት ማርኪያ መሆን ማስቆም የምንችለው እኛው ብቻ ነን። ወገኖቻችን በረሃብ አለንጋ እየረገፉና ነፍስ አድን የምግብ እርዳታ ከፈረንጅ በምጽዋት እየተቸረን በምድራችን የሚመረት እህል ባህር አቋርጦ ለባለጸጋ አገሮች ገቢያ ሲውል አይተን እንዳላየን ማለፉን ማስቆም የኛ ተግባር ነው። ዕዳው ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ የብድር ገንዘብ በየአመቱ አገር ውስጥ በገፍ እየገባ እናቶችና ህፃናት በንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረት መሰቃየታቸውን ማስቆም የምንችለው እኛው ነን። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናት በቂ የትምህርት እድልና የጤና አገልግሎት የሚያገኙበት ገንዘብ በሙስናና በሌብነት በተጨማለቁ የአገዛዙ ሹመኞች መዘረፉን ማስቆም ያለብን እኛው ነን።

"ውሃ የለም መብራት የለም ኑሮ ከአቅማችን በላይ ሆኖ መኖር አቅቶናል" የሚለውን የወገን እሮሮ ያሰሙ ልጃገረዶችን ድምጽ መስማት ግዴታችን ነው። የእነዚህ ወጣቶች አርዓያነትን በመቀበል ዛሬውኑ የትግሉን ጎራ በመቀላቀል አብሪተኛውንና ዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ ፍጻሜ በማፋጠን ነፃነታችንን እንድንጎናጸፍ ግንቦት 7 የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የወያኔ ጄኔራሎች እርስ በርሳቸዉ እየተተራመሱ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሀገር እየተንከራተተ ሃላፊዎች እና ኀጠኞች እየተንደላቀቁ ከፍተኛ ሃብት አፍርተዋል የሚል ጉምጉምታ በወታደሩ ሰፈር መነሳቱና ይህም ለሳሞራ በጥያቄ መልክ ከቀረበ በኋላ እንደሆነ ታውቋል። በዚህ የተነሳም ይህን ጥያቄ እንዲነሳ ያደረጉት የአማራና ኦሮሞ ከፍተኛ አመራሮች ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ እንደተደረሰም ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ጨምረው ገልጸዋል። የሲቪል ስልጣንን ምክንያት ያደረገው ይህ የሹም ሽር በወታደሩ ሰፈር ከተሰማ በኋላ ከፍተኛ ውጥረትና መደናገጥ እንደተፈጠረም ታውቋል።

አማራና ኦሮሞ ጄኔራሎችንና ከፍተኛ ወታደሮችን ለማጥራት ምሎ የተነሳው ሳሞራ ከዚህ በፊት በአማራና በኦሮሞ ወታደሮች ላይ በመዘባበት የትእቢት ንግግር ሲየደርግ የነበረ ሲሆን ይህንኑ ለከት የለሽ ንግግሩን በመቀጠል ሰሞኑን ዩኒፎርሙን ሽጦ ካልጠታበት አንድ ጉራጌ ጄኔራል ሹመናል ማለቱ አይዘነጋም።

## ሃያ ሦስት የስቃይ፤ የሰቆቃና የእልቂትና ዓመታት

የኢትዮጵያ ህዝብ በፋሽስቱ ህወሓት ብልሹ አስተዳደርና አምባገነናዊ አገዛዝ ስር ወድቆ በኑሮ ውድነትና በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱ ተነጥቆ ለአፈናና ለእስራት እየተዳረገ፣ ሉዓላዊ ክብሩ ተደፍሮ ለም መሬቱንና አንጡራ ሃብቱን እየተሸነሸነና እየተቦረቦረ ለባዕድ እየተሸጠ፣ በገዛ ሀገሩ ተፈናቃይና የውጭ እጅ ተመልካች ሆኖ ለስደትና ለእንግልት እየተዳረገ እነሆ ዛሬ ከ23 ዓመት በላይ የሰቆቃ፣ የእልቂትና የመከራ ዓመታት ተቆጠሩ።

ለአለፉት 23 ዓመታት የደፈረሰው ፖለቲካችን ወደ ጭቃነት እየተቀየረ ስለመሆኑም ምንም ምስክር አያሻውም።ፋሽስቱ ወያኔ ከሀገር ሉዓላዊነት እስከ ታሪካችን፣ ከባንዲራችን እስከ እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር ያለን ደረጃ መቀመቅ አውርዶታል። አንዳንዶቻችን እንደዚህ ዘመን ትውልድ አባልነታችን ያለፈውን መለወጥ፣ ዛሬን የሰውነት ደረጃችን በጠበቀ ሁኔታ መኖርና ነገንም ላልተወለዱ ልጆቻችን መልክ አስይዞ ለማውረስ ከቁጥጥራችን እየወጣ መሆኑን በግልጽ እንመለከታለን። በሌላ ወገን ወያኔዎቹ የአለፉት 23 ዓመታት የአንድ ጀምበር ያህል አጥረውባቸው፤ ተጨማሪ 40 አመታትን ለመግዛት በማለም ሲንፈራገጡና በቀቢጸ ተስፋ ህዝብን ለማማለል ሲሞክሩ እያየንና እየሰማን ነው። ስንራብ መጥገባችንን ይነግሩናል። ስንታረዝ ደራርበን መጎናፀፋችን ይታያቸዋል። ሀገራችን ከአለም ሀገሮች ተርታ በሁሉም መስኮች ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ በማይታመን ፍጥነት እየወጣች ወደ ግርጌ ስትወረወር፤ ወንበዴዎቹ ወያኔወች ግን ሀገራችን ተሞሸረች አማራች ይሉናል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲረግጡት የሚደቅን ቅጠል ያህል በመቁጠር ከህግና ከአመክንዮ ውጭ በማን አለብኝነት ሕዝባችንን በንግድ ድርጅቶቻቸው እየገፈፉ እርቃኑን አስቀርተውታል።

ጉጅሌው ወያኔ ሥልጣን ሲይዝ፣ ከፎከረባቸው አንዱ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን ሶስቴ የሚበላበትን ሁኔት ፈጥሮ ከረሀብ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚገላገልበትን ባዶ ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር። ነገር ግን ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን ሶስቴ አበሳውን እየበላ ይገኛል። ምግብማ ከየት ተገኝቶ! ረሀቡ፣ ጠኔው ከዛሬ ሀያ ዓመት ሁኔታ በሶስት ዕጥፍ ጨምሮ፣ ዛሬ እስከ 25 ሚሊዮን ሕዝብ ጦሙን የሚያድርባት አገር ስለሆነች በየጊዜው የተባበሩት መንግስታትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሚያወጡት መግለጫ መረዳት ይቻላል። ዛሬማ፣ ነጻ ገበያ ብሎ የፎከረብን ነጻነት ተረስቶ የዘይትና የስኳር ዋጋ እስከመቆጣጠር ገብቷል። ከመብራት፣ ውሃና ኔትዎርክም ብሶ ህዝብ በእጦት ከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ይገኛል። በቅርቡም በመላ ሃገሪቱ መብራት፣ ውሃና ኔትዎርክ እጦትን አስመልክቶ ሰልፍ ሊወጣ ቅድመ ዝግጅቶች እየተገባደዱ እንደሆነም እየተሰማ ነው። ከዚህ በላይ የጨለማ ጊዜ የለም።

የወያኔ አገዛዝ ለአለፉት 23 ዓመታት የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ በመስጠትም በተደጋጋሚ ብሄራዊ ክህደት ሲፈጽም የቆየ ቡድን ነው። ይህንን ብሄራዊ ክህደት ሲፈጽም ካለማወቅ፤ ከችኮላ ወይም በደመነፍስ ከመጓዝ የተሠራ ስህተት አይደለም። ከአጠቃላይ የፓለቲካ ስትራተጂውና ግብ ጋር የተያያዘ አካሄድ ስለመሆኑ መስካሪ አያሻም። ፋሽስቱ ህወሓት በህዝብ የተተፋ ቡድን በመሆኑ የሀገሪቱን ፓለቲካና ኤኮኖሚ ለመቆጣጠር የውጭ ኃይሎችን የገንዘብ፤ የወታደራዊና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ስለሚሻ ነው የሀገሪቷን ብሄራዊ ጥቅሞች መረን በለቀቀና ድፍረት በተሞላበት መልክ ለውጭ ኃይሎች በየጊዜው አሳልፎ የሚሰጠው።ለዚህም ነው የምግብ እጥረት ያለባት የሀገራችንን ሰፋፊ ድንግል መሬቶቿን ለሀገሪቷ ዜጎች ከልክሎና አፈናቅሎ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለእስያ ሀገሮች ልማታዊ ድርጅቶች በነፃ በሚባል ደረጃ እስከ 99 ዓመት በሚደርስ ውል ፈርሞ እየሸጠ የሚገኘው። ሰፊ ለም የድንበር መሬታችንንም ቆርሶ ለባዕዳን በመሸጥ ላይም ለመሆኑ ከሰሞኑ ለሱዳን ተላልፎ የተሰጠው መሬት ማስረጃ ነው።

በርግጥ የተደራረበ ጭቆናና መከራ ያንገሸገሸውና በልቡ የሸፈተው ህዝብ የጥቂት አምባገነኖችና ሰው በላ መሪዎች የባርነት ቀንበር ተሸክሞ ዘላለም መኖር እንደማይችል ግልፅ እየሆነ መጥቷል። በመሆኑም እንደ እሳተ ጎመራ ውስጡ ውስጡን እየተብላላ ቆይቶ ዛሬ ሊፈነዳ የተቀራበውን የህዝብ ዓመፅ መለብለብ የማይቀርላቸው መሆኑን በውል የተረዳው የጉጅሌው ወያኔ ቡድን ከመቼውም በላይ በፍርሃትና በጭንቀት ተውጠው እንዳበደ ውሻ መቅበዝበዝ፣ መወራጨት፣ መናከስና መተራመስ እንደ ጀመሩ በጋሃድ እየታየ ነው። ባለፈው ሳምንት በሰማያዊ ፓርቲ ሴት አመራርና አባላት መሪነት የታየውን አመጽ ተከትሎ ፋሽስቱ ወያኔ የወሰደው እርምጃ ለዚህ በቂ ማሳያ ነው። ሌላው የአዋጅ ጋጋታ፣ የዉሸት እምብልታ፣ ዜጎችን ያላንዳች ምክንያት ማስፈራራት፣ እስር ቤት ማጎር፣ ማሳደድ፣ መግረፍና ማፍን የመሳሰሉ የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዎች በግልፅ የሚያሳዩን የስርዓቱን መፈረካከስና የውድቀቱን ዋዜማ መቃረቡን ነው።

ስለዚህ ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን በሞት ጣር ላይ ሆኖ እያቃሰተ የሚገኘውን አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቅበር መፍትሄው በእጃችን ነው ይላል። ግንቦት 7 መፍትሔው ስለጨቀየው ፖለቲካ እያወሩ ፈጣሪ ባመጣው ይመልሰው ማለት አይደለም ብሎ በፅኑ ያምናል። መፍትሔው እርስ በእርሳችን ስንወጋገዝ መኖርም ሳይሆን ልዩነቶቻችን በማጥበብ፤ ጠብታዎች ባህር እዲሆኑ ማድረግ ነው። መፍትሔው እጅን አጣምሮ ጥቂቶች ታምር እንዲሰሩ መጠበቅም አይደለም። መፍትሔው ከያንዳንዳችን የሚጠበቀውን ሌላውን ሳንጠበቅ መወጣት እንጂ። ስለዚህ አምባገነኖችን መካብ ዙፋናቸውን አግዝፎ በመመልከት ከትግል መሸሽ የችግሩ መፍትሔ በጭራሽ ስለማይሆን ኑ! ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አገዛዙን ከህዝብ ጫንቃ ለማውረድና ሃገርን ለማዳን እያደረገ ያለውን ትግል ይቀላቀሉ በማለት ሃገራዊ ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል።

## ደሃዉ ኢትዮጵያዊ ለመለስ ፋውንዴሽን ገንዘብ እንዲያዋጣ እየተገደደ ነው

በ20 አመት የስልጣን ዘመኑ የኢትዮጵያን ህዝብ እጅና እግር አስሮ እያሰቃየ ለገዛዉ መለስ ዜናዊ ፋዉንዴሺን ማሰሪያ እየተባለ ያ ተረግጦ የተገዛዉ ህዝብ ገንዘብ ካላዋያህ እየተባለ በወያኔ ካድሬዎች እየተሰቃየ መሆኑን በየክልሉ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። የወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎች በተለይ በአዲስ አበባና በአጎራባች ከተሞች ከቤት ወደ ቤት እየዞሩ ለመለስ ፋውንዴሽን ማቋቋሚያ ከ50 ብር ጀምሮ እንዲከፍሉ እያስገደዱ ነው። እድሮች በነፍስ ወከፍ ከ8 ሺ ብር ጀምሮ እንዲከፍሉ መመሪያ ተላልፎላቸዋል።

በዚህ መመሪያ የተሰላቹና የተበሳጩ ሰዎች “ወዴት እንሂድ” ሲሉ ለኢሳት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። የመለስ ፋውንዴሽን በወ/ሮ አዜብ መስፍን ሊቀመንበርነት የሚመራ ሲሆን የአቶ መለስን አስከሬን በቋሚነት የሚያርፍበትን ቦታ የማዘጋጀትና ስራዎቻቸውን ለህዝብ የማቅረብ አላማ አለው። ምንም እንኳ መንግስት ለፋውንዴሽኑ ማሰሪያና ስራ ማስኬጃ በየአመቱ ገንዘብ የሚሰጥ ቢሆንም፣ ይህ ሳያንስ እያንዳንዱ ህዝብ ገንዘብ እንዲያወጣ መገደዱ አግባብ አለመሆኑን አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። ገንዘብ መስጠትም ካለባቸው የኢህአዴግ ደጋፊዎች እንጅ ኢህአዴግን የማይደግፉት እንዲሰጡ መገደድ የለባቸውም ሲሉ እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

## በኩዌት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የተሞላ በመሆኑና የአገዛዙን ገጽታ ለመጠበቅ በሚል በየጊዜው በመኪና ተገጭተው፤ ታንቀውና ራሳቸውን ከፎቅ በመወርወር የሚያጠፉና የሚገደሉ ኢትዮጵያውያን ደብዛቸውን እያጠፉ እንደሚገኙ በማጋለጥ የሞት ጉዳያቸው እንዳይነሳ በመሸፋፈናቸው የብዙ ወገኖቻችን ደም በከንት ፈሶ እየቀረ ነው ሲሉ ምሬታቸውን ገልፀዋል።

የኩዌት መንግስት ስለ ግድያው መንስኤ እስካሁን በኦፊሴል ያሳወቀው ነገር ባይኖርም የኩዌት የፓርላማ አባላትና አንዳንድ ባለስልጣናት ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው እንዲወጡ እየወተወቱ እንደሚገኙ ታውቋል። ጉጅሌው ወያኔ በቅርቡ በሳውዲ አረቢያ እንደተመለከትነው የወገኖቻችን ሰቆቃም ሆነ ግድያ ቁብ የማይሰጠው በመሆኑ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁኔታውን በንቃት እንዲከታተሉት ጥሪ ቀርቧል።

## የአባይ ግድብ መዋጮ መቀዝቀዙ ወያኔን ስጋት ላይ ጥሎታል

በመዋጮ፤ በቦንድ ሽያጭና በቁጠባ ከህዝብ በሚገኝ ገንዝብ ይሰራል ተብሎ የዛሬ ሦስት አመት ግንባታዉ የተጀመረዉ የአባይ ወንዝ ግድብ በያዝነው ወር የሶስተኛ ዓመት የምስረታ ልደቱ በዐሉ እየተከበረለት ቢሆንም ለገድቡ ግንባታ እስከዛሬ ከወጣዉ ወጪ ከህዝብ መሰብሰብ የተቻለዉ ይገኛል ብሎ ከተጠበቀዉ 26% ብቻ ፤መሆኑ ወያኔን ከፍተኛ ስጋት ላይ እንደጣለዉ ታወቀ። ይህ በመጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በቀድሞ ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የመሰረት ድንጋይ ተጥሎለት በይፋ ግንባታው የተጀመረዉ ግድብ ገና ከመሰረቱ ዋናዉ የገንዘብ ምንጩ ሕዝቡ እንደሚሆን የተነነገረ ሲሆን በዚሁ መሰረት በተለይ የመንግስት ሠራተኛውና ባለሃብቱ ሳይወድ በግድ እንዲያዋጣ ሲደረግ ቆይቷል።

ለግድቡ ግንባታ በጠቅላላው ከ80 ቢሊየን ብር በላይ የሚያስፈልግ መሆኑንና እስካሁን ለግድቡ ግንባታ 27 ቢሊየን ብር ገደማ ከመንግስት ካዝና መውጣቱን ተነግሮአል። ባለፉት ሶስት ዓመታት ከሕዝቡ ቦንድ ለመግዛት ቃል የተገባው 11.5 ቢሊየን ብር ሲሆን መሰብሰብ የተቻለው ግን 7.1 ቢሊየን ብር ብቻ ነው።

መዋጮው የመንግስትና አንዳንድ የግል ድርጅት ሠራተኞች ሳይወዱ በግድ ከፔሮላቸው በየወሩ እየተቆረጠ ገቢ የሚሆን በመሆኑ አብዛኛው መዋጮ የተሰበሰበው ከወርሃዊ ደመወዝተኛው መሆኑ ከግንባታው ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ አመልክቶአል። አብዛኛው ባለሃብትና ነጋዴዎች ከንግድ ሰርዓቱ መዛባትና ከስርዓቱ ኢ-ፍትሐዊ እርምጃዎችጋር በተያያዘ እንዲሁም የቦንድ ሰርተፍኬቱን ለባንክ ብድር ማስያዝ ካለመቻላቸው ጋር ተያይዞ የገቡትን ቃል መፈጸም እንደተሳናቸው ታውቆአል።

የቦንድ ሽያጩን በውጪ አገር የሚኖረው ዲያስፖራ እና በገጠር የሚኖረው አርሶአደርና አርብቶአደር የህብረተሰብ ክፍልን በማሳመን ለማስፋት ዕቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ ቢደረግም በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ባለማግኘቱና በተለይ የአርሶአደሩ ገቢ ከእጅ ወደአፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መሳካት አለመቻሉ ታውቆአል።በውጪ አገር የሚኖረው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ መቅደም ያለበት የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው በሚል አገዛዙ ከኢሰብዓዊ ድርጊቶቹ እንዲቆጠብ በተደጋጋሚ መጠየቁ የስርኣቱን ከፍተኛ አመራሮች ባለማስደሰቱ ከገቢ ማሰባሰቡ ስራ እንዲያፈገፍጉ ምክንያት መሆኑ የሚታወቅ ነው።

በአገር ውስጥ በተለይ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የግድቡ ግንባታ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እየተጠቀመበት በመሆኑና ስለጉዳዩም የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማሳተፍ ፍላጎት አለማሳየቱ በብዙዎቹ ዘንድ ጉዳዩ በአሉታ እንዲነሳ እያደረገው ይገኛል። በዚህም ምክንያት ለግድቡ መዋጮ የህዝቡ መነሳሳት እንዲቀዛቀዝ ምክንያት መሆኑ ይታወቃል። በተያያዘ ዜና ከግብጽ መንግስትና ፖለቲከኞች ጠንካራ ተቃውሞ እየቀረበበት የሚገኘውን የአባይ ግድብ ዓለምአቀፍ ጋዜጠኞችን ለማስጎብኘት የኢትዮጵያ መንግስት ጥሪ ማቅረቡ ተሰማ። በዚሁ መሠረት 13 ያህል ዓለም አቀፍ የፕሬስ ተቋማት ፍላጎት ማሳየታቸውንና በቅርቡ ጉብኝቱ እንደሚካሄድ ታውቋል።

## አዲስ አበባ ዉስጥ በትራፊክ አደጋ የሚሞቱ ዜጎች ቁጥር በሚያስፈራ መልኩ እያደገ ነዉ

የኢትዮጵያ መዲና የሆነቸዉ አዲስ አበባ ዉስጥ በየቀኑ በትራፊክ አደጋ የሚኖተዉ ሰዉ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መምጣቱን ከአፋቸዉ እዉነት ወጥቶ የማያዉቀዉ የወያኔ ባለስልጣኖች ጭምር በመናገር ላይ መሆናቸዉን የአዲስ አበባ ዘጋዎቻችን ከሰሞኑ በላኩልን ዜና ገለጹ። የትራፊክ አደጋዉ አዲስ አበባን ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ዙሪያና በዋና ዋና የከተማዋ መግቢያ በሮችም በየቀኑ እንደሚከሰት ዘጋቢዎቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል። በአሁኑ ግዜ አዲስ አበባ ዉስጥ በአንድ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ብቻ የትራፊክ አደጋ በየቀኑ የሶስት ሰዎችን ህይወት እንደሚቀጥፍ ለማወቅ ተችሏል። ከከተማዋ ነዋሪ ቁጥርና ከተማዋ ዉስጥ ከሚገኘዉ አጠቃላይ የመኪና ብዛት ጋር ሲታይ አዲስ አበባ ዉስጥ በየዕለቱ የሚደርሰዉ የመኪና አደጋና የሚሞተዉ ሰዉ ቁጥር እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ።

አንድ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዶ/ር ዳንኤል ረዳ የተባሉ ምሁር ባቀረቡት ጥናታዊ መረጃ መሰረት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የተሽከርካሪ ብዛት 344,108 ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ከግማሽ በላዩ ወይም 55.7% የሚሆነዉ የተሽከርካሪ ብዛት የሚገኘዉ አዲስ አበባ ዉስጥ ነዉ። በዶ/ር ዳንኤል ጥናት መሰረት ኢትዮጵያ ዉስጥ እያንዳንዱ አንድ ሺ ኢትዮጵያዊ 3.8 መኪናዎች ያመለክታል. በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔ ባለስልጣኖች በሚያወጡት መረጃ መሰረት አዲስ አበባ ዉስጥ ብቻ በየቀኑ ከ5 ሰዉ በላይ በመኪና አደጋ ይሞታል። ይህ ቁጥር እጅግ በጣም አሳሳቢ የሆነ ቁጥር ነዉ ይላሉ አንድ የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር በሰጡት አስተያየት።

የወያኔ ሚዲያዎች በየቀኑ እንደሚገልጹት በከተማዋ የሚከሰተው የትራፊክ አደጋ ቁጥር ከመቼውም በላይ እየጨመረ ሲሆን ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው ለመንገደኛ ቅድሚያ መከልከል፣ርቀትን ጠብቆ አለማሽከርከር፣ቁም የሚል ምልክት አልፎ መሄድ፣ የአሽከርካሪ ብቃት ማነስ፣ወደ ግራና ቀኝ ያለጥንቃቄ መታጠፍ፣ ርቀትን ጠብቆ አለማሽከርከር ናቸው። ይሁን እንጅ በቅርቡ የተደረጉት ጥናቶች እንደሚያመላክቱት በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ከመቼውም በተለየ አኳኋን እየተካሄ ባለው ሰሞነኛ የዘመቻ ግንባታ ማለትም የቤቶች፣የመኪና መንገድና የባቡር መንገድ ስራዎች በርካታ ዜጎች በመኪና እንዲገጩ ምክንያት እየሆነ ነው።

ዋና የመኪና መንገዶች ለዕድሳት በሚል እየፈራረሱ በአጥር መታጠራቸው፣ በየአካባቢው ለግንባታ ግብዓት አቅርቦት በሚል በአሸዋና ድንጋይ ክምር መዘጋታቸው፣ በመንገድና በድልድይ ፍርስራሾች ማስተንፈሻ አማራጭ መንገዶች ሳይቀሩ መዘጋታቸው፣ ለግንባታ ሂደት የሚያግዙ አዳዲስና አሮጌ ከባድ የጭነት መኪኖች ለረጂም ሰዓታት ሲቆሙ መንገዶች መጨናነቃቸው፣ ማስተንፈሻ ተብለው የተመደቡ መሿለኪያ መንገዶች የሚገኙት በነዋሪዎች ሰፈር በመሆኑና ስፋታቸው አነስተኛ መሆኑ የከተማው ተሽከርካሪዎች ባሉበት መንገድ ላይ ለረጅም ሰዓት መኪኖች እስከሚያልፉ ለመቆም በመገደድ ነዋሪዎቹ ለአደጋ ይጋለጣሉ።

የአዲስ አበባ ብዙ መንገዶች ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ እየተዘጉ ነው። በመኖሪያ ሰፈር ስር ባሉ ጠባብ መሿለኪያ መንገዶች ሰውና መኪኖች የሚጋፉባት፣ ድንገት በሚንሻራተቱና በሚናዱ መንገዶች ከቀላል እስከ ከባድ መኪና የሚጓዙባትና መኪና በየጊዜው የሚገለበጥባት፣ ጠባብ ድልድዮች ላይ መኪኖች ተደርበው የሚያልፉባት፣ በድንገት የመኪና ብልሽት አጋጥሞ መኪና ከቆመ አንድ መንገድ ላይ ተቆሞ የሚዋልባት ከተማ ሆናለች። በከተማዋ የሚገኙት ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ተሽከርካሪዎች በብቃት መመዘኛ በዓለም ገበያ ላይ ምርታቸው የቆመ፣ ከተበላሹ መለዋወጫ የሌላቸው፣በብቃት ማነስ በየቦታው አደጋ የሚያደርሱ፣ ያለ በቂ ፍተሻ ከውጭ ተገዝተው የሚገቡ፣ የብቃት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ናቸው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የወያኔ አገዛዝ የግብር ፖሊሲ አርሶ አደሩንና ነጋዴዉን እያሰቃየ መሆኑ ተነገረ

የወያኔ አገዛዝ የሚከተለዉ የግብር ተመንና አሰባሰብ ፖሊሲ አብዛኛዉን የኢትዮጵያ ግብር ከፋይ እያሰቃየ መሆኑን ከኢትዮጵያ የሚመጡ መረጃዎች ያሳያሉ። የግብር ፖሊሲዉ በተላይ የገበሬዉንና የነጋዴዉን ህብረተሰብ ከመጠን በላይ እያስጨቀ መሆኑን አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙ ነጋዴዎች ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ስልክ እየደወሉ በመናገር ላይ ናቸዉ። ለምሳሌ ከአገር ዉስጥ ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰቡ መረጃዎች አንደሚያሳዩት  የኦሮምያ፤ የአማራና የደቡብ ክልል አርሶ አደሮች ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ወስዳችሁ ግብርና የወሰዳችሁትን የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ዋጋ አንክፍልም ብላችኃል በሚል ታስረዉ ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑ ተመልክቷል።

“በእድሜ የገፉ እናት አባቶችን ታስረው ይንገላታሉ ፤ ከብቻችንን ከቤታችን በሃይል ነድተው ያስራሉ ፤ በሬ ከቀንበሩ ፈተው ይወስዳሉ፣ የታጠቁ የመንግስት የፀጥታ ስተዳደር እና ሚልሻዎች በአርሶ አደሩ ላይ ድብዳ ይፈጽማሉ” ሲሉ አርሶደሮች ተናግረዋል። በጎጃም አካባቢ የመንግስት ታጠቂዎች ክፍያውን እናስከፍላለን በሚል ከእርሻ ላይ በሬ ለመፍታት ባደረጉት ሙከራና፣ በሬዎቼን ከቀንበር ላይ አላስፈታም ባለ  አርሶ አደር መካከል በተፈጠረ ውዝግብ፤ የአምስት ሰዎች ህይዎት  ጠፍቷል። በግጭቱ የሞቱት አርሶ አደር በሪሁን ፈንታ፣ ባለቤቱና የመጀመሪያ ልጁ ሲሆኑ፣ ሁለት ደግሞ የመንግስት ታጣቂዎች ናቸው።

የመንግስት ከሚዩኒኬሺን ጽ/ቤት መረጃ እንደሚያሳየው ባለፈው ዓመት በነበረው የአካባቢ ምርጫ፣ ህዝቡ ከምርጫ ውጭ እንዳይሆን በማሰብ የማዳበሪያ እና የግብር እዳ ሳይጠየቅ ከርሟል። በኦሮምያ ላሞቻቸውን በእዳ አስረክበው 13 ወጣቶች መሰደዳቸውን፣በአማራ ክልል 57 ወጣቶች መሸፈታቸውን፤ በደቡብ 31 አርሶ አደሮች እርሻ አቁመው ሎሌነት መቀጠራቸው በጥናቱ ተመልክቷል።በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ገዢው ፓርቲ ከአርሶ አደሩ የሚያገኘው ድምጽ አይኖርም ብሎአል ሪፖርቱ። ኢህአዴግ  አርሶ አደሩን ግብር ለማስከፈል አዲስ እንቅስቃሴ ለመጀመር ቢያስብም፣ መጪውን ምርጫ በመፍራት ለጊዜው ለመተው እንደወሰነ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሰሞኑን በግብር አከፋፈል ዙሪያ ላይ በባህር ዳር ከተማ የኢፌዴሪ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ባካሄደው ስብሰባ ላይ ነጋዴዎች ምሬታቸውን  ሲገልጹ ተደምጠዋል። በስብሰባው ላይ በአማራ ክልል ንግድና ዘርፍ ማህበራት አማካኝነት የተካሄደ ጥናት የቀረበ ሲሆን፣ በጥናቱምው በግብር ሰብሳቢውና በግብር ከፋዩ መካከል ያለው ግንኙነት መሻከሩ ተመልክቷል።የግብር ስርአቱ አገልግሎት አሰጣጥ የፍትህዊነት ችግሮች ያሉበት በመሆኑ በነጋዴውና በመንግስት መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር አድርጓል። የመንግስት አካላት የሚወስዱት እርምጃ ፈተና እንደሆነባቸው የተናገሩት ነጋዴዎች በ25 ብር ቅጣት  ለአመት የታሰሩ  ነጋዴዎች አሉ ብለዋል።

ባጠቃላይ በግብር ምክንያት በመላ ሃገሪቱ ባሉ ትልልቅ ከተሞች 7 ሺ 943 ሰዎች በእስር ላይ እንደሚገኙ በሪፖርቱ ተመልክቷል። አንድ በቆዳ ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለሀብት አግባብ ባልሆነ መንገድ 2 ሚሊዮን ብር የግብር ወለድ እንዲከፍሉ መገደዳቸውን ገልጸዋል። የፍትህ ተቋማት መንግስት ይዞ የሄደውን ብቻ የሚወስኑ፣ የነጋዴውን ጉዳይ ዘወር ብለው የማያዩ በመሆኑ ፍትሃዊ ውሳኔ ለማግኘት መቸገራቸውንም ነጋዴዎች ገልጸዋል። በግብር አስገቢ መ/ቤቱ ብቻ ሳይሆን በግብር ከፋዩ በኩልም የሚታዩ ችግሮችን የዳሰሰው ጥናቱ ግብርን ለመክፈልና በዝምድናና በትውውቅ ለመስራት መሞከር እንዲሁም ህገ ወጥ ነጋዴዎችን ለማጋለጥ አለመፈለግ ይታይባቸዋል ብሏል።

## ሀረር ከተማ በሳምንት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የእሳት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሰሞኑን በሀረር ከተማ የደረሰውን ተደጋጋሚ ቃጠሎም ጸረ ሰላም ሃይሎች አደረሱት ለማለት እየተንደረደረ መሆኑ ቃጠሎውን የፈጸመው እራሱ ወያኔ መሆኑን ሊደብቅለት አይችልም የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም።

በተያያዘ ዜና ከፍተኛ ጭንቀት በነጋዴዎች ላይ በመፈጠሩ በተለይም "የላይኛው ታይዋን " የእሳቱ ቀጣይ መዳረሻ ሊሆን ይችላል የሚሉ ጥቆማዎች በስፋት በመነገራቸው በንግድ ማዕከሉ የሚሰሩ ነጋዴዎች ንብረታቸው እያሸሹ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። በስፋት መወያያ የሆነው ይህ "የላይኛው ታይዋን" የተባለው የገበያ ማእከል እጣ ፈንታ ህዝቡን ስጋት ላይ የጣለ ሲሆን የፋሽስቱ ወያኔ ፖሊሶችም በህዝቡ ደህንነት ላይ ተጽዕኖ እየፈጠሩ መሆናቸው ታውቋል።

ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ የተለያዩ የሕዝብ የገበያ መእከሎችን በማቃጠል ራሱ በፈጠራቸው ጸረ ሰላም ሃይሎች ሲያመካኝ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ታላላቅ ሆቴሎችን፣ የሕዝብ ማመላለሻ መኪኖችንና ሌሎችንም የሕዝብ ሃብቶች ራሱ በቦንብ በማፈንዳት መልሶ በሌሎች ላይ ጣቱን ሲቀስር እንደነበርም አይዘነጋም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሀረር ላይ እንደገና የደሰዉን  የእሳት ቃጠሎ አስመልክቶ የከተማዉ ነዋሪ ህዝብና የወያኔ አገዛዝ የቃላት እሩምታ እየተለዋወጡ መሆኑን ከስፍረዉ የደረሰን ዜና ያስረዳል። ህዝቡ ወያኔን ለቃጠሎዉ ተጠያቂ ሲያደርግ፣ ወያኔ ደግሞ በበኩሉ ድብቅ የፖለቲካ አላማ ያላቸው ሀይሎችን ያደረሱት ቃጠሎ ነው ይላል። አብዛኛው የሃረር ህዝብ እሳት አደጋው መንስኤ መስተዳደሩ ነው ብሎ ያምናል። የመስተዳድሩ ባለስልጣናት ቦታዎችን ለሚፈለጉ ሰዎች ለመስጠት በማሰብ ቃጠሎውን እንደሚያስነሱ ይገልጻሉ። የሃረሪ መስተዳድር የኮሚኒኬሽን ቢሮ በበኩሉ “ከደረሰው አደጋ ጋር በተያያዘ ህዝብና መንግሥትን ለማጋጨትና ድብቅ የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማራመድ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን ከመንግሥት ጎን በመሆን እንታገላቸዋለን” በማለት የእሳቱን መንስኤ በስም ያልተጠቀሱት ድብቅ ሃይሎች ያስነሱት ነው በማለት በመስተዳድሩ ላይ የሚሰነዘረውን ወቀሳ ለማስተባበል ሞክሯል።

በመጀመሪያው ቃጠሎ ወቅት ብስጭታቸውና ቁጣቸውን ለመግለጽ ወደ አደባባይ የወጡ የሃረር ወጣቶች በፖሊሶች ተደብድበው ሲበተኑ ከ40 ያላነሱ ወጣቶች ደግሞ በቁጥጥር ስር ውለው እስከ ዛሬ አልተፈቱም። ባለፈው ቅዳሜ የተነሳውን እሳት ሰበብ በማድረግ ዝርፊያ ሊፈጽሙ ሲሉ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች መታሰራቸውን የመስተዳድሩ ሹማምንት ለመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ሲገልጹ፣ ነዋሪዎች በበኩላቸው ከፍተኛውን ዝርፊያ ሲፈጽሙ የነበሩት ፖሊሶች ናቸው ይላሉ። እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት ፖሊሶች በተለይም የሞባይል ስልኮችን ሲያሸሹ ነዋሪው በትዝብት ያያቸው ነበር።